# በወቅታዊ የሃገራችን ሁኔታ ካይ የሚካሄድ ኮንፈረንስ ከአትላንታ
# የህብረቱ ደጋፊ ኮሚቴ

አሁን ያለንበት ወቅት የሃገራችን ኢትዮጵያና የህዝብዋ ጉዳይ በጣም አሳሳቢ የሆነበት ደረጃ ነው። ዛሬ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም ዙሪያ የምንወያይበት ወቅት አይደለም። ህዝባችን መብትና ስልጣኑን ተነጥቆ ግፍና በደል እየደረሰበት በመሆኑ በምንጨነቅበት ወቅት ጭራሽ የከፋ የጦርነት ደመና የዕልቂት ዘመቻ በሃገራችን ሉዓላዊነት በህዝባችን አንድነትና ደህንነት ላይ እያንዣበበ ነው።

ይህን አደጋ ቀድመን ልንከላከለው ይገባል፣ ከዚህ አንፃር በአትላንታ የኅብረቱ ድጋፍ ኮሚቴ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት፣ ሃገር ወዳዶችና ምሁራን እንዲሁም የሁሉም የሃይማኖት ተወካዮች የሚሳተፉበት ኮንፈረንስ በማዘጋጀት ላይ ነው። ይህ ኮንፈረንስ የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተኛል ለሚሉ ኃይሎች በሙሉ መድረክ በመፍጠር በጆርጂያና በዙሪያዋ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ውይይትና ምክክር በማድረግ ሃገራችን ከጥፋት ህዝባችንን ከእልቂትና ከመከፋፈል ለማዳን ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ታስቦ የተዘጋጀ በመሆኑ ጥሪያችን በአካባቢያችን ለሚገኙ ድርጅቶች ተወካዮች በማስተላለፍ ልዩ ዝግጅት በማድረግ ላይ ነን። በዚህ ዝግጅት እኛም (እኔም) ለህዝብና ለሃገር የሚጠቅም መልዕክት አለኝ የሚሉ ኃይሎችን በሙሉ ለማስተናገድ የምንሞክር ስለሆነ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ኃይሎች በሙሉ ጥሪያችንን እያስተላለፍን ከዚህ በታች በተገለፁት ስልክ ቁጥሮች የሚፈልጉትን ማብራሪያ ማግኘት እንደሚችሉ እንገልፃለን።

ኮንፈረንሱ የሚካሄደው December, 30 2006 ሲሆን ዝርዝር ፕሮግራሙ ወደፊት ይገለፃል።

404 931-2655
678 791-5580

ሃገራችንን ከጥፋት ህዝባችንን ከእልቂት ለማዳን በአንድነት እንነሳ!!
የህዝባችን መብትና ስልጣን ይረጋገጥ!!
ሁሉም የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች ይፈቱ!!

ከአዘጋጅ ኮሚቴው።